# ያ ትውልድ

ቀን ፡ ጥቅምት ፰ ቀን ፪ ሺህ ፰ ዓ.ም. (October 18, 2015)

## በጎጃም ክ/ሀገር ደብረማርቆስ የደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊ የነበረው አረመኔ የደርግ አባል ፻ አለቃ እሸቱ ዓለሙ በቁጥጥር ሥር ዋለ

*ከ«ያ ትውልድ ተቋም» የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ*

የከበረ ሰላምታችንን በቅድሚያ አያቀረብን፤

ደም ያዘለ ዶሴ፤ ልዩ አቃቤ ሕግ ጽ/ቤት ዘገባ ጥር 2002 ዓ.ም. አዲስ አበባ።

ከአገኘነው የ፻ አለቃ እሸቱ ዓለሙ የወንጀል ዘገባ የቀነጨብነውን በማቅረብ እንጀምራለን።

ቴሌግራም 28.5.70 ከም/መ/አለቃ እሸቱ ዓለሙ ለብሔራዊ አብዮታዊ ዘመቻ መምሪያ እንዲያውቁት ለሻምበል ፍቅረስላሴ፤ ፀረ-ሕዝቦችን ለመመንጠር በኦፕሬሽን ላይ ነኝ:: . . . በዛሬው ዕለት በ7 ሰዓት ሁለት የፖሊስ አባሎች አንድ ሻምበል ሌላው የአስር አለቃ . . . ላይ እርምጃ ተወስዷል:: . . . ሁለቱም ተገድለዋል:: ሴሚናሩና ምንጠራው አሁንም እንደቀጠለ ነው እስከ ነገ ድረስ ሁሉም ተይዘው እስካለቁ ድረስ ኦፕሬሽኑ ይቀጥላል:: ም/መ/አ እሸቱ ዓለሙ

በፋይል ይቀመጥ:: ፊርማ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ 4.6.70[114]

ለጎጃም ክፍለሀገር ወህኒ ቤቶች አስተዳደር ጽ/ቤት ደብረማርቆስ:-

ስማቸው ከዚህ ጋር ተያይዞ በተላከልዎት ዝርዝር የተገለፀው 80 /ሰማንያ/ ፀረ-አብዮተኞች ፀረ-አብዮት ድርጊታቸው በጣም ከፍተኛ በመሆኑ አብዮታዊ እርምጃ እንዲወሰድባቸው ሆኖ አፈፃፀሙ እንዲገለፅ ያደርጉ ዘንድ አስታውቃለሁ 8/12/70 ም/መ/አ እሸቱ ዓለሙ የክፍለሀገሩ ቋሚ የደርግ አባል፣

ለጓድ መቶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ
የጎጃም ክፍለሀገር ቋሚ የደርግ አባል ደብረማርቆስ[115]

በ8/12/70 በቁጥር 448/4/11 በተፃፈልን ትዕዛዝ መሰረት 71 ፀረ-አብዮተኞች አብዮታዊ እርምጃ ሲወሰድባቸው፣ ሶስቱ ቀደም ሲል ከወህኒ ቤት፣ ሲያመልጡ የተገደሉ አንድ በዚሁ ቀን የጠፋ፣ አምስቱ ግን በመተከል አውራጃ ወህኒ ቤት የሚገኙ መሆኑን እየገለፅን ዝርዝሩን በዚህ ደብዳቤ አማካይነት መላካችንን እናሳስባለን:: ኢትዮጵያ ትቅደም ወንድምዬ ኃይሌ ኮለኔል የጎጃም ክፍለሀገሮች ወህኒ ቤቶች ዋና አስተዳዳሪ:-[116]

**በጎጃም ክፍለ ሀገር ደብረማርቆስ ከተማ በ1969/70/71/72 የደርግ ቀይ ሽብር ዘመቻ ዋና ተዋናይ የነበረው ነብሰ ገዳይ የደርግ አባል የ፶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ በቁጥጥር ሥር መዋሉ ተዘገበ።**

**በኔዘርላንድ አንድ የደች ጋዜጣ** October 16, 2015 (http://www.rtvnh.nl/nieuws/172574/Man) **እንደተዘገበው የኔዘርላንድ ዜግነት ይዞ አድፍጦ የነበረው ይህ የደርግ ቀይ ሽብር ተሳታፊ አምስተልቨን በምትባል የኔዘርላንድ ከተማ በቁጥጥር ሥር ውሏል።**

**የ61 ዓመት ዕድሜ እንደሆነ በጋዜጣው የተዘገበው እሸቱ ዓለሙ በጎጃም ደብረማርቆስ በመቶዎች የሚቆጠሩ ወጣቶችን በደርግ ቀይ ሽብር ዘመን የፈጀ አረመኔ ነበር። የ፶ አለቃ እሸቱ ዓለሙ አሁን ባለው አገዛዝ በሌለበት የሞት ፍርድ የተፈረደበት ወንጀለኛ ነው።**

የበርካታ ወጣቶችንና ጎልማሶችን ደም እንደውሃ አፍስሦ ምንም እንዳልሰሩ አድፍጦ መቀመጥና ይባስ ብሎ ያንን ትውልድ ተጠያቂ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫና ታሪክ ብረዛ ተከላካይና ሀቁን አስረጂ ወገን እንዳለው ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም።

የከፍተኛ ዘጠኙ ገዳይ ቀልቤሳ ነገዎ፣ የከፍተኛ 15ቱ ከፈለኝ ዓለሙን ጨምሮ ሰሞኑን በቁጥጥር ሥር የዋለው የጎጃም ደብረማርቆሱ የደርግ አባል የ፲ አለቃ እሸቱ ዓለሙ መሰል ገዳዮችን ማንነት በማጋለጥና ጉዳያቸው ለፍርድ ይቀርብ ዘንድ ጥረትና ትብብር ያደረጋችሁ የያ ትውልድ አባላት ምስጋና ይገባችኋል። በየቦታው አድፍጠው ያሉ የደርግ ኢሠፓ ነብሰበላዎችንና የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጪና አስፈፃሚዎችን ለፍርድ ማቅረብ እንጂ ጊዜው የእኛ ነው ብሎ በየፖለቲካው መድረኩ ላይ ይጨፍሩ ዘንድ ዕድል መስጠት በሰማዕታት ወገኖቻችን ደምና አጥንት ዳግም መጨፈር እንደሆነ በዚህ አጋጣሚ «ያ ትውልድ ተቋም» ያስገነዝባል።

የ፲ አለቃ እሸቱ ዓለሙን ጉዳይ በመከታተል ጊዜያችሁንና አቅማችሁን አስተባብራችሁ ጥረት ላደረጋችሁት ወገኖች በ«ያ ትውልድ ተቋም» ስም እያመሰገንን በቀጣይነትም ለሚካሄደው የፍርድ ሂደት ሙሉ በሙሉ ከጐናችሁ መሆናችንን ስናሳውቅ በታላቅ ደስታ ነው።

በጎጃም ደብረማርቆስ ባህርዳርና አካባቢው በአረመኔው ኮ/ል ተካ ቱሉና የ፲ አለቃ እሸቱ ዓለሙ የተጨፈጨፋችሁ ብርቅዬዎች፣ በደርግ የአንድ ትውልድ መመተር ቀይ ሽብር ጥቃት ሰለባ ለሆናችሁ ቤተሰቦችና ወገኖች በሞላ፡ የዛሬ 38 ዓመት በማንሃህሎኝነት በየእሥር ቤቱና በየመንገዱ የፈሰሰው የልጆቻችሁ ደም ሰሚ ሊያገኝ ችሏል። ጊዜው ምንም ቢርቅ ጉዳዩ ዛሬም ያንገበግባልና ወንጀላቸውን ተሸክመው ማንነታቸውን ደብቀውና አድፍጠው ያሉ ገዳዮች ምንጊዜም፣ ዛሬም ወደ ፊትም ወደ ሕግ በማቅረብ ለሌሎች ትምህርት ሊሰጥ ይገባዋል እንላለን። ጊዜ የሰጠውን ጉልበትና ኃይል ተጠቅሞ ያለአግባብ የሚፈስ የንጹሃን ደም ሌላ ጊዜ የፍትህ ያለህ ብሎ ወደ ሕግ እንደሚያቀርበው ትምህርት ሊወሰድበት ይገባል። ዛሬ ዓለም የወንጀለኞችና የገዳዮች ዋሻ አለመሆኗን በትንሹም ቢሆን ግንዛቤ በመውሰድ ከተደበቁበት ዋሻ ወደ አደባባይ በማውጣት ማንነታቸውን ማሳወቅ የታሪክና የትውልድ አደራን መወጣት ነው እንላለን።

በ1969/70/71/72 ዎቹ የደርግ ቀይሽብር ተሳታፊዎች ጉዳይ የሁላችንም የያ ትውልድ አባላትና ቤተሰቦች የጋራ ኃላፊነት በመሆኑ በየቦታው አድፍጠው የተቀመጡትን በደም የተነከሩ ወንጀለኞች ቢያንስ በኅብረተሰቡ ሊታወቁ የሚገባቸው በመሆኑ የጉዳዩ ባለቤት ሁላችንም ነንና፤ ድጋፍና ትብብራችን ለግለሰቦችና ለተወሰኑ አካላት ሳይሆን ለሚነሳውና ለተነሳው ጉዳይ መሆኑን በማገናዘብ ድምጻችንን በጋራ እናሰማ እንላለን።

በደርግ ቀይ ሽብር የተጨፈጨፉ ሰማዕታት ምንጊዜም አንረሳቸውም!!!
የጊዜ መርዘም ከወንጀል ነፃ አያደርግም!!!

«ያ ትውልድ ተቋም»

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com, yatewlid@hotmail.com
web site : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org
Facebook: yatewlid